# የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል ስለተዘጋጀው አዋጅ ረቂቅ የቀረበ

# አጭር መግለጫ

<u>ጥር 2015 ዓም</u>

# 1. መግቢያ

የኤክሳይዝ ታክስ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ተብለው ከሚታወቁት በዕቃ እና በአገልግሎት ላይ ከሚጣሉት ታክሶች ምድብ ውስጥ የሚገኝ ታክስ ነው፡፡ የኤክሳይዝ ታክስ ዋንኛ ዓላማዎች ለመንግሥት ተጨማሪ ገቢ ማስገኘት፣ በኅብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ምርቶችን ፍጆታ መቀነስ፣ ከፍተኛ ሀብት ያላቸው ሰዎች ከሚጠቀሙባቸው የቅንጦት ዕቃዎች ላይ ገቢ በመሰብሰብ በድህነት ውስጥ የሚገኙ ዜጐችን ሕይወት ማሻሻል እንዲሁም በአካባቢ ደህንነት (environment) ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ምርቶችን አጠቃቀም መቀነስ ናቸው፡፡

የኤክሳይዝ ታክስ በማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ ቦታዎች እንዲሁም ዕቃዎች ወደአገር በሚገቡበት የጉምሩክ ጣቢያ የሚሰበሰብ ሲሆን፣ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ እንደመሆኑ አምራቹ፣ አስመጪው ወይም አገልግሎት ሰጪው በዕቃው ወይም በአገልግሎቱ ዋጋ ላይ በማከል መንግሥትን በመወከል ከተጠቃሚው ሰብስቦ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ የሚያደርገው የታክስ ዓይነት ነው፡፡ ታክሱ የሚጣለው እንደሁኔታው በዕቃ ወይም በአገልግሎት ዋጋ ላይ በመቶኛ (advalorem) ወይም በዕቃው መለኪያ በኪሎ፣ በብዛት ወ.ዘ.ተ ላይ በመመስረት በቁርጥ በሚወሰን የገንዘብ መጠን (specific) ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ሥራ ላይ ያለው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ከየካቲት 5 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለ ሲሆን፤ አዋጁ፤ ከሌሎች መካከል፤ የታክሱን መሰረት በማስፋት፤ የታክሱን አስተዳደር ስርዓት በመቀየር፤ በአካባቢ ደህንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማስከተል ላይ የሚገኙት ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወደአገር እንዳይገቡ በማድረግ፤ ወዘተ. ከፍተኛ ጠቀሜታን አስገኝቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአዋጁ በተደረጉት ለውጦች ምክንያት መንግሥት ከኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበስበው ገቢ በወቅቱ የገበያ ዋጋ በ55% ከፍ ያለ ሲሆን በተከታታይ በየዓመቱ እየቀነሰ በመሄድ 0.6 የአገር ውስጥ ምርት ድርሻ ደርሶ የነበረው ከኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበሰበው ገቢ በተደረገው ማሻሻያ ለመጀመሪያ ጊዜ ዕድገት ማሳየት መቻሉ ሪፎርሙ ውጤታማ መሆኑን ያሳያል፡፡

ታክስ ለመንግሥት ገቢ ከማስገኘት በተጨማሪ ኢኮኖሚውን የመምራት ድርሻ ስላለው የኢኮኖሚውን እንቅስቃሴ በመከተል የታክስ ሕጎች በየጊዜው ማሻሻያ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኞዎቹ የአለም አገሮች በየአመቱ የበጀት ዝግጅት በሚደረግበት ጊዜ የታክስ ሕጎቻቸውን በመፈተሽ አስፈላጊውን ማሻሻያ ያደርጋሉ፡፡ በአገራችንም በተመሳሳይ ሁኔታ የኢኮኖሚውን አቅጣጫ በየጊዜው በመዳሰስ የታክስ ሕጎቻችን የኢኮኖሚውን ዕድገት በሚያግዝ እና የመንግሥትንም ወጪ መሸፈን በሚያስችል አኳኋን በተወሰነ ጊዜ ልዩነት እንዲሻሻሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም

የኤክሳይዝ ታክስ በየበጀት ዓመቱ አስፈላጊውን የአፈፃፀም ፍተሻ በማድረግ በዳሰሳ ማስተካከያ ማድረግ በሌሎች ሀገሮች የተለመደ ነው።

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ያስገኘውን ጠቀሜታ እንዲሁም ያስከተለውን ችግር በሚመለከት ዝርዝር ጥናት የተደረገ ሲሆን፤ ከላይ እንደተገለፀው የአዋጁ አፈፃፀም የሚያበረታታ ሆኖ ተገኝቷል። ይሁን እንጂ አንዳንድ የማስከፈያ መጣኔዎች በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ተወዳዳሪነት ላይ ጫናን ያሳደሩ በመሆኑ ለዚህ ችግር መፍትሄ ለማስገኘት፤ በአንዳንድ ምርቶች ላይ የተጣለውን የተጋነነ የማስከፈያ መጣኔ በማስተካከል እንዲሁም በአንዳንድ አገልግሎቶች ላይ ታክሱን በመጣል የመንግሥትን ገቢ ለማሳደግ እንዲቻል በአዋጁ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 2. <u>የማሻሻያው ዋና ዋና ገጽታዎች</u>

### 2.1 <u>በተሽከርካሪ ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ ማሻሻል</u>

ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች በአካባቢ ደህንነት እና በትራፊክ አደጋ ከሚያስከትሉት ጉዳት በተጨማሪ ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ እና የመለዋወጫ ወጪ የሚጠይቁ በመሆኑ ወደአገር እንዳይገቡ ለመከላከል የሚያስችል ከፍተኛ ታክስ የተጣለባቸው ሲሆን፤ አዋጁ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ያገለገለ ተሽከርካሪ ወደአገር የማስገባቱ ተግባር ተቋርጧል።

ከዚህም ጋር ተያይዞ እስከ 1300 ሲ.ሲ. ያላቸው አዲስ ተሽከርካሪዎች ወደአገር እንዲገቡ ለማበረታታት በእነዚህ ተሽከርካሪዎች ላይ ተጥሎ የነበረው 30% የኤክሳይዝ ታክስ ወደ 5% ዝቅ እንዲል ተደርጓል።

ይሁን እንጂ ከ1300 ሲ.ሲ. በላይ ባላቸው አዲስ ተሽከርካሪዎች ላይ ተመሳሳይ ቅናሽ ባለመደረጉ የዚህ አይነቶቹ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች በሚፈለገው መጠን ወደአገር የማይገቡ ከመሆኑም በላይ መንግሥት ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወደአገር እንዳይገቡ በመደረጉ ያጣውን ገቢ ለማካካስ አልተቻለም።

ከዚህም በተጨማሪ በአገራችን ስራ ላይ ባሉ ሕጎች በተሽከርካሪ ላይ የተጣለው ቀረጥ እና ታክስ በድምር ሲታይ እንደተሽከርካሪው አይነት ከ66% እስከ 374% የሚደርስ ሲሆን፤ በጎረቤት ኬንያ ከፍተኛው መጣኔ 96%፤ በሩዋንዳ 71.3% እና በጋና 40%፤ ብቻ ነው። ይህም በአገራችን በተሽከርካሪ ላይ የተጣለው ቀረጥ እና ታክስ ከልክ በላይ የተጋነነ መሆኑን ያሳያል።

በሌላ በኩል በአለማችን ለቀረጥ አከፋፈል ሲባል የሚደረገው የተሽከርካሪ አመዳደብ ወደአራት ምድብ የተቀየረ በመሆኑ፤ አገራችንም ይህንን ምደባ ተከትላ የታሪፍ አወቃቀርዋን ማስተካከል ይኖርባታል፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች፤

- የተሽከርካሪ አመዳደብ ከ1500 ሲ.ሲ. በታች፤ ከ1501-2500 ሲ.ሲ.፤ ከ2501-3000 ሲ.ሲ. እና ከ3000ሲ.ሲ. በላይ በሚል እንዲስተካከል፤

- አዳዲስ ተሽከርካሪዎችን በሚመለከት ፤ከ1500 ሲ.ሲ. በታች የሆኑት 10%፤ ከ1501-2500 ሲ.ሲ. 20%፤ ከ2501-3000 ሲ.ሲ. 30% እና ከ3000 ሲ.ሲ. በላይ የሆኑት 60% የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልባቸው፤ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

ይህ ማሻሻያ በአዲስ ተሽከርካሪ ላይ የተጣለውን ቀረጥ እና ታክስ ድምር እንደተሽከርካሪው አይነት የሚቀንስ ሲሆን ከ3000 ሲ.ሲ. በላይ የሆኑት አዲስ ተሽከረካሪዎች ላይ የሚከፈለው ቀረጥ እና ታክስ ድምር 121% እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ማሻሻያው ከፍተኛ አቅም ባላቸው ተሽከርካሪዎች ላይ ከፍተኛ ቅናሽ የሚያስከትል ቢሆንም፤ ከጎረቤት አገሮች ጋር ሲነፃፀር አሁንም ከፍተኛ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ወደአገር ከሚገባው የተሽከርካሪ አይነት እና ብዛት አንፃር ሲታይ ማሻሻያው መንግሥት በአመት 5.5 ቢሊዮን ብር ገቢ እንዲያጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ሆኖም ታክሱ ሲቀንስ ወደአገር የሚገቡት የዚህ አይነት ተሽከርካሪዎች ቁጥር ሊጨምር ስለሚችል መንግሥት የሚያጣው ገቢ ከ 2.1- 3.3 ቢሊዮን ብር እንደሚቀንስ ይገመታል፡፡

## 2.2 <u>ተደራራቢ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ምርቶች ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ ማሻሻል</u>

በህበረተሰቡ ጤና እና ማህበራዊ ኑሮ ላይ ችግር የሚያስከትሉትን የሲጋራን እና የአልኮል መጠጦችን ፍጆታ ለመቀነስ ሲባል ለእነዚህ ምርቶች ማምረቻ በሚውል ትምባሆ፤ ንፁህ አልኮል እና ስኳር ላይ ታክስ የተጣለ ሲሆን፤ በመጨረሻው ምርትም ላይ ታክስ ይከፈላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 14(2) አልኮል፤ ትንባሆ እና ስኳር ላይ የተከፈለ የኤክሳይዝ ታክስ በመጨረሻው ምርት ላይ የሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ በሚሰላበት ጊዜ ተቀናሽ እንደማይደረግ ተመልክቷል፡፡

ለእነዚህ ምርቶች ማምረቻ በሚውለው ግብዓት እና በመጨረሻው ምርት ላይ የሚከፈለው ታክስ ከፍተኛ በመሆኑ በተወዳዳሪነታቸው ላይ ከፍተኛ ጫናን

አስከትሏል። በተለይም በንፁህ አልኮል ላይ 60% የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለ ሲሆን፤ በሚጠጣ አልኮል ላይ 80% የተጣለ በመሆኑ ታክሱ በዘርፉ ላይ ከፍተኛ ጫናን አሳድሯል።

በሌላ በኩል ከውጭ አገር ባለቀለት ምርት ደረጃ የሚመጡ የአልኮል ምርቶች በመጨረሻው ምርት ላይ ብቻ ታክስ የሚከፈልባቸው በመሆኑ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ተወዳዳሪ ሊሆኑ አልቻሉም። ይህንን ችግር ለማስወገድ በንፁህ አልኮል ላይ የተጣለው 60% ወደ 10% ዝቅ እንዲል ሀሳብ ቀርቧል።

በተመሳሳይ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ስኳር የታከለባቸውን ምርቶች የሚያመርቱ እንደ ከረሜላ ያሉ ኢንዱስትሪዎች በስኳር ላይ ከሚከፍሉት የኤክሳይዝ ታክስ በተጨማሪ በምርቱ ላይ የሚከፍሉት 20% ከፍተኛ በመሆኑ ወደ 10% ዝቅ እንዲል ሀሳብ ቀርቧል።

## 2.3 <u>ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ሰዎች በሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግ፤</u>

በመግቢያው እንደተገለፀው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በአመዛኙ በአካባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት በሚያስከትሉ ምርቶች ላይ ነው። በመሆኑም በእነዚህ ምርቶች የሚጠቀም ሰው በአካባቢ ላይ በሚያደርሰው ጉዳት የተነሳ ህብረተሰቡ ከሚያጋጥመው የጤና ችግር ለመታደግ እና ለአካባበቢ ጥበቃ መንግሥት የሚያወጣውን ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል ገቢ በኤክሳይዝ ታክስ አማካኝነት ይሰበሰባል።

እስከሁን በነበረው አሰራር በልዩ ሁኔታ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ዕቃዎችን ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲያስገቡ ሲፈቀድ ይህ ፈቃድ የኤክሳይዝ ታክስንም የሚጨምር ስለነበር መብቱ የተፈቀደላቸው ሰዎች እና ድርጅቶች በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ዕቃዎችን ወደአገር በማስገባት ለሚያደርሱት ጉዳት ማካካሻ የሚሆን ታክስ አይከፍሉም። ይህ አሰራር ተገቢ ባለመሆኑ ኢትዮጵያ ባደረገችው አለም አቀፍ ስምምነት ከተፈቀደው በስተቀር በኢንቨስትመንት ማበረታቻም ሆነ በሌላ ተመሳሳይ ልዩ ፈቃድ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ወደአገር የሚያስገቡ ሰዎች ወይም ድርጅቶች በተመሳሳይ በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ በመሆኑ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍሉ ማድረግ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህም መሰረት ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 1 ከታክሱ ነፃ ተደርገው ከነበሩት መካከል መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፤ በኢንቨስተሮች፤

በአካል ጉዳቶኞች፤ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ የተዘረዘሩ ተቋማት የሚያስመጧቸው ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ መደረጋቸው እንዲቀር ሀሳብ ቀርቧል፡፡

## 2.4 በቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ላይ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈል ማድረግ፣

ከኤክሳይዝ ታክስ አላማዎች አንዱ ለመንግሥት ገቢ ማስገኘት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ መንግሥት በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ጫናን ሳይፈጥር ገቢ ሊሰበስብ ከሚችልባቸው የስራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ነው፡፡

ይህም በመሆኑ በርካታ የአለም አገሮች ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የኤክሳይዝ ታክስ ይሰበስባሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ጎረቤታችን ኬንያ ከቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት 10% የኤክሳይዝ ታክስ በማስከፈል ላይ ትገኛለች፡፡ በመሆኑም እያደገ የመጣውን የመንግሥት የወጪ ፍላጎት ለማሟላት ጫና በማይፈጥር ዝቅ ባለ መጣኔ ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ላይ የኤክሳይዝ ታክስ መሰብሰብ ተገቢ ይሆናል፡፡

በመሆኑም ከቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት 5% የኤክሳይዝ ታክስ እንዲሰበሰብ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

## 2.5 የኤክሳይዝ ታክስ ተጥሎባቸው ከነበረ አንዳንድ ምርቶች ላይ ታክሱን ማንሳት

በስራ ላይ ባለው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ታክሱ ከተጣለባቸው ምርቶች መካከል የቪዲዩ ካሜራ እና ቴሌቪዥን ይገኙበታል፡፡

በቪዲዮ ካሜራ ላይ የተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ከሁለት አመታት በፊት ከ40% ወደ 10% ዝቅ የተደረገ ቢሆንም በማደግ ላይ የሚገኘው የፊልም ኢንዱስትሪ ባለበት የገንዘብ አቅም ውስንነት እንዲሁም የቅጂ መብት ያለመከበር ባሳደረበት ተጽህኖ ምክንያት ይህም ወጪ ከዘርፉ አቅም በላይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ለኪነጥበብ ዕድገት መንግሥት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ስላለበት ታክሱ ሙሉ በሙሉ ቀሪ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ሆኖ ተግኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ቴሌቪዥን በዋንኛነት የመረጃ እና የእውቀት ማሰራጫ በመሆኑ በቴሌቪዥን ላይ የተጣለውን ታክስ በማንሳት ህብረተሰቡ ዝቅ ባለ ዋጋ የቴሌቪዥን ባለቤት እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በቴሌቪዥን ላይ ተጥሎ የነበረው 10% የኤክሳይዝ ታክስ እንዲነሳ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

## 2.6 በአስተዳደር ችግር ምክንያት የተደረጉ ማስተካከያዎች

ከታክስ መርሆዎች አንዱ የታክስ ስርአቱ ለማስተዳደር የሚያመች መሆን አለበት የሚል ነው። ይሁን እንጂ በኤክሳይዝ አዋጅ ከተጣሉ ታክሶች ውስጥ ወስጥ በሰንጠረዡ ተራ ቁጥር 15.16 ለምግብነት በተዘጋጀ ከ100 ግራም ውስጥ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ የአትክልት እና የእንስሳት ዘይት የተጣለው ታክስ ለማስፈጸም አስቸጋሪ ሆኖ በመገኘቱ ተግባራዊ ሳይደረግ ቆይቷል።

ለዚህም ዋንኛው ምክንያት በአገር ውስጥ በሚመረተው እንዲሁም ከውጭ ወደአገር ከሚገባው ምርት ውስጥ የተጠቀሰውን ያህል ስባት ያለውን የመለየቱን ተግባር ያከናውናል ተብሎ የነበረው የምግብ እና የመድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን እና አምራች ፋብሪካዎች ይህንን ለማከናወን የሚያስችል አቅም ያልገነቡ መሆኑ ነው።

በመሆኑም ታክሱን ለማስተዳደር የሚያስችል አቅም የሌለ መሆኑ በጤና ሚኒስቴር የተረጋገጠ ስለሆነ ለጊዜው ከሰንጠረዡ እንዲወጣ ተደርጓል።

በሌላ በኩል በጨው ላይ ታክሱ ሲሰበሰብ የቆየው በየኬላው በኩንታል በተወሰነ መጣኔ ሲሆን፤ ይህም መጣኔ በአዋጁ ከተጣለው መጣኔ አንጻር ሲታይ አነስተኛ ነው። በመሆኑም በመጣኔው ላይ የተደረገው ጭማሪ የጨው ዋጋ መናርን ሊያስከትል ስለሚችል ማስተካከያ ተደርጎበታል።

ስለዚህ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ የቀረበው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ በስራ ላይ እንዲውል እንዲፈቀድ ይህ አጭር መግለጫ ቀርቧል።

# አዋጅ ቁጥር ________/2015

## የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ወደአገር በሚገቡ አዲስ ተሽከርካሪዎች እና አንዳንድ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን እጅግ በጣም ከፍተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በልዩ ሁኔታ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ሰዎች እና ድርጅቶች በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ በመሆኑ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ጭምር ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው እንዲያስገቡ መፍቀድ ተገቢ ባለመሆኑ፤

የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልበት ማድረግ መንግሥት ለሚያከናውናቸው የልማት ስራዎች የሚውል ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኝ መሆኑ ስለታመነበት፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) እና (11) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ አዋጅ "የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ (ማሻሻያ) ቁጥር _____/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>**ማሻሻያ**</u>

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2020 (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፤

1. ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (22) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (23)፣ (24) እና (25) ተጨምረው በነባሩ ከንዑስ አንቀጽ (23)-(34) የሆኑት እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (26)-(37) ተደርገው ተሸጋሽገዋል፤

"23. "**ኤቲይል አልኮል**" ማለት ጥራቱ 80 ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ አልኮል ነው፤"

"24. "**አዲስ ተሽከርካሪ**" ማለት ከተመረተበት ዓመት ጀምሮ ከዚህ በታች ከተመለከተው በላይ አገልግሎት ያልሰጠ ተሽከርካሪ ሲሆን፤ የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ. በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠም ሙሉ በሙሉ ተበትኖ ወደአገር የገባ ወይም በከፊል ተበትኖ ወደአገር የገባ ተሽከርካሪ፤

ለ. በጉምሩክ ታሪፍ በአንቀጽ 87.02፣ 87.03፣ 8704፣ 87.05 እና 87.11 የሚመደብ ሆኖ፤ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥሞ ወደአገር የገባ፤ በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) በደረሰበት ጊዜ የተመረተበትን የዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ በጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ዕድሜው ከሶስት ዓመት የማያልፍ እና ከውጭ አገር እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) ድረስ የተነዳው ርቀት ከ4,000 ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፤

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ "ለ" በታሪፍ አንቀጽ ተለይተው ከተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች ውጪ በሚሆንበት ጊዜ ተሽከርካሪው የተመረተበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ በሚቆጠር በአራት የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) የደረሰ ነው፡፡"

"25. **"ያገለገለ ተሽከርካሪ"** ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (24) ለአዲስ ተሽከርካሪ በተሰጠው ትርጉም የማይሸፈን ተሽከርካሪ ሲሆን፤ የአገልግሎት ዘመኑም ተሽከርካሪው የተመረተበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) የደረሰበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ይጨምራል፡፡"

2. የአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፤

"2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 በተደነገገው መሰረት ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 1 የተዘረዘሩት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች በሰንጠረዡ በተመለከተው የማስከፈያ ልክ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡"

3. የአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው ተራ ፊደል (ሀ) ተተክቷል፡

"1. (ሀ) ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 2 የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ዕቃዎች፤"

4. ከአዋጁ አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ (4) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) ተጨምሯል፤

"5. ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት የባንክ ፈቃድ አግኝተው ከማናቸውም ቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ዕቃዎች ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ወደአገር የሚገቡ ከሆነ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይደረጉባቸውም፡፡"

3. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ቀን**</u>

ይህ አዋጅ ከ______ቀን 2015 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ____ቀን 2015 ዓ.ም.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## <u>ሠንጠረዥ ሁለት</u>

### ክፍል አንድ
### <u>ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች</u>

የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ተደርገዋል፡፡

1. አውሮፕላን በዓለምዐቀፍ ትራፊክ እንቅስቃሴ ውስጥ ባለበት ጊዜ ተሳፋሪ መንገደኞች እና የአውሮፕላኑ ሠራተኞች በጉዞ ወቅት የሚጠቀሙባቸው በነፃ የሚሰጡ ዕቃዎች፣

2. የዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱለር ሚሲዮኖች ወይም ዲፕሎማቶች እና ቆንስላዎች ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ የዲፕሎማቱ እና የቆንስላው ቤተሰቦች ወደአገር የሚያስገቧቸው ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዟቸው በዲፕሎማቶች መብትና ጥቅም ደንብ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

3. በመንግሥት ጥሪ መሰረት በአደጋ የተጐዱ ሰዎችን ለመርጃ እንዲውሉ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች፣

4. የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ወይም የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች ወደአገር የሚያስገቧቸው ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዙዋቸው በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣

5. ከተሽከርካሪ በስተቀር ወደአገር የሚገቡ መንገደኞች ይዘዋቸው የሚመጡ አግባብ ባለው ሕግ የተፈቀዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፤

### ክፍል ሁለት
### <u>ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ አገልግሎቶች</u>

የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ተደርገዋል፤

- ለዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱለር ሚሲዮኖች ወይም ዲፕሎማቶች እና ቆንስላዎች ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ የዲፕሎማቱ እና የቆንስላው ቤተሰቦች የሚሰጡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች፤

**PROCLAMATION NO_____/2022**

**EXCISE TAX (AMENDMENT) PROCLAMATION**

**WHEREAS**, it has become necessary to lower the exaggerated excise tax rate imposed on imported new vehicles and some other items;

**WHEREAS**, it is found not proper to grant persons and organizations with special tax and duty privileges to also import goods on which excise tax is imposed because of the damage they inflict on the environment free of excise tax;

**WHEREAS,** it is believed that imposing excise tax on telecommunication services will help generate more revenue to finance development activities carried out by the Government;

**NOW THERFORE**, in accordance with Article 55(1) of Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Excise Tax (Amendment) Proclamation No. ___/2022".

**2. Amendment**

The Excise Tax Proclamation No. 1186/2020 (as amended) is hereby further amended as follows:

1. The following new sub-articles (23), (24) and (25) are added after sub-article (22) of Article 2 and the existing sub-articles (23)-(34) are renumbered from (26)-(37) respectively:

"23. "**Ethyl alcohol**" means alcohol of purity of 80 degrees or more;"

"24. "**New Vehicle**" means a vehicle that has not been used over what is stated in this sub-article since its manufacturing year and includes the following:

a. imported in semi-knocked Down (SKD) or Complete Knocked Down (CKD) form to be assembled by local industry ;

b. a Complete Built Up (CBU) vehicle of tariff heading 87.02, 87.03, 87.04, 87.05 and 87.11 which arrives at the Ethiopian customs territory (entry point) within a time period of three Gregorian calendar years including the manufacturing calendar year of the vehicle and when the number of kilometers driven abroad at the time it arrives at the Ethiopian custom territory (entry point) does not exceed 4,000 kilometers;

c. If the vehicle is not covered under sub-letter (b) of this sub-article it arrives at Ethiopian custom territory (entry point) within a time period of four Gregorian calendar years including the manufacturing calendar year of the vehicle;"

“25. “ **Used Vehicle**” means a vehicle not covered under sub-article 24 of this Article and the age is counted beginning the manufacturing Gregorian calendar year to the Gregorian calendar year of its arrival at Ethiopian customs territory (entry point);”

2. Sub-Article (2) Article 5 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article 2:

   “2. Excise Tax shall be charged at the rate specified in the first Schedule attached herewith for the excisable goods and services in force at the time the liability arises for excise tax as determined under Article 9 of this Proclamation.”

3. Sub-article 1 (a) of Article 8 is deleted and replaced by the following new “a’:

   “a. exempt goods which meet the conditions set out under the Second Schedule attached with this Proclamation;”

4. The following new sub-article (5) is added after sub-article (4) of Article 43

   “ 5. Excise tax on goods to be imported into Ethiopia free of any taxes and duties, for which bank permit has been obtained prior to the enactment of this Proclamation and imported within two months from the effective date of this Proclamation shall be assessed and collected in accordance with the Excise Tax Proclamation No. 1186/2020 (as amended).”

**3. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on this ____day of _______2022.

Done at Addis Ababa this ____day of ____2022.

SAHLEWORK ZEWDE
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## SECOND SCHEDULE
## PART A

## EXEMPT EXCISABLE GOODS

The following excisable goods shall be exempt from excise duty:

1. Excisable goods that are bona fide stores for aircraft, being goods for use or consumption by passengers or crew of aircraft while on board and while the aircraft is in international traffic;
2. Excisable goods imported into Ethiopia or purchased in Ethiopia by a diplomatic or consular mission, or by a diplomat or consul, or a member of the diplomat or consul's family forming part of the diplomat or consul's household in Ethiopia to the extent provided for under the Privileges and Immunities Regulations;
3. imported consignments for emergency relief in response to an emergency call issued by the Government;
4. All goods imported or purchased locally for the official use by the Ethiopian Defense Forces and the Federal and State Police Commissions as provided in a Directive issued by the Minister;
5. Excisable goods except vehicle imported by, and in the possession of a passenger subject to limitations provided for in the appropriate law.

## PART B
## EXEMPT EXCISABLE SERVICES

The following excisable services shall be exempt from excise duty:

- Excisable services supplied in Ethiopia to a diplomatic or consular mission or to a diplomat or consul, or a member of the diplomat or consul's family forming part of the diplomat or consul's household in Ethiopia to the extent provided for under the Privileges and Immunities Regulations.